# በአሮጌ አቁማዳ አዲስ ወይን ጠጅ!!!

## *ስድብ የሃሳብ እጦት ውጤት!*

ከኃይለገብርኤል

አይጦች የድመት ጥቃትና ወረራ ለማስወገድ ስብስባ ይቀመጡና መፍትሄ ለማፈላለግ ይሞክራሉ ።በዚህ የአይጦች ውይይት ድመትን ለማስውገድ ሰፊ ዳሰሳ ተደርጎ ይህ ነው የሚባል መፍትሄ አጥተው ሊበተኑ ሲቃረቡ አንድ ጎረምሳ አይጥ ሃሳብ አለኝ ይልና ይፈቀድለታል። ጎረምሳውም አይጥ ድመት አንገት ላይ ቃጭል ማንጠልጠል ብንችል አስቀድመን መንቃትና ከጥቃት ለማምለጥ ያስችለናል የሚል ሃሳብ ያቀርባል። መፍትሄ አጥቶ ግራ ሲጋባ የነበረው ጉባኤተኛ ሃሳቡን በጋለ ስሜት አጨብጭቦ ይቀበላል ። ከእድምተኛው አንዱ ይነሳና ፤ ሃሳቡ መልካም ነው ፤ መንገዱ ግን አደገኛ ነው ፤ ቃጭሉን በድመቱ አንገት ላይ የሚያስሩ ጎበዞች ከመካከላችን ያሉ አይመስለኝም ሲል አስተያየት ያቀርባል። ያኔ ተደፈርን ባዮች አስተያየት የሰጠውን አይጥ ክብራችንን ነካህ ሰንፎች አድርገህ ዘለፍከን ሲሉ ከያቅጣጫው በስድብና እርግማን ወረዱበት ከስበሰባውም አዳራሽ ገፋፍተው ወደ ደጅ አውጥተው ጣሉት።

ይህን በስሜት የተሞላ የጀማውን ሁኔታ በአንክሮ ሲከታተሉ የቆዩ አዛውንት ይነሱና እንዲህ ለክብራችንና ለደህንነታችን በመቆርቆር ያሳያችሁት ወኔ የሚደነቅ ነው ፤ ሲሉ ሙገሳ ካቀረቡ በሗላ ፈቃደኛ የሆነ ካለ በቅድሚያ እድል ይሰጠው አልያም ጎበዞችን ወደ መምረጡ እንሂድ ብለው ተቀመጡ። ያኔ ማን ጎበዝ ይገኝ? ማን ሃላፊንት ይውሰድ? ሁሉም ጸጥ ረጭ አለ! በመጨረሻም የተግባር ስራውን ለመፈጸም የሚችል ወኔ ያለው አንድም አይጥ ባለመገኘቱ ያ ረጅም ሰአታት የወሰደ ስብሰባ በጉራና በስሜት የተሞላ ፉከራ ያለ አንዳች መፍትሄ ተበተነ። ቆራጥነትና የተግባር ታጋይን ያጣው የአይጥ መንጋ ታድኖ ወደ መበላቱ ወደ ጭቆናና ባርነቱ ተምልሶ ለዘለዕለም ተሳዳጅና ምርኮኛ ሆኖ ቀረ ይባላል ።

የተረቱ ባለቤት የኛ አባቶች ይሁኑ የውጭ ሰዎች ባላውቅም ፤ በአንድ መጽሄት ላይ ማንበቤን አስታውሳለሁ። እናም በአንድ ጎኑ አሁን እኛ ኢትዮጵያውያን ካለንበት ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ይመሳሰልብኛል። መቼም እንደ ሠው ማሰብ የሚችል አይጥ ባይኖርም እንደ እይጦቹ ግን የሆኑ ሰዎች ማየት የተለመደ ሆኗል። እይጥ የራሱ ያልሆነውን የሰው ሌማት ከፍቶ የሚችልውን በልቶና የቀረውንም አበላሽቶ መሄድ ተፈጥሯዊ ባህሪው ነው። በዚህ ዘመን ያውም በሰለጠነው አለም ፖለቲካዊ ተሳትፎ አድራጊ ነን በሚል የሌሉበትን የፖለቲካ ድርጅት ሊያፈርሱ የማያባራ አሉባልታ ማራባትና ፤የነሱ ያልሆነን ሕዝበዊ ተቋማት ለመናድ እረፍት ማጣት አየጎለበተ የመጣ ባህል ሆኗል። ያልወደዱትን ግለሰብ ስም ለማጉደፍ የማይቀባጥሩት አሉባልታና ያማይነዛ የስድብ አይነት ሳይበሩን አጨናንቆት ይታያል ።

የማህበራዊ ሚድያ መድረክ የታደሉት ለዘመናት ተጭኖአቸው የኖረን አንባገነን አገዛዝ ለመገርሰስ ተጠቀመውበታል። ያልታደለ በእርስ በርስ ሽኩቻ አብሮነቱ አላልቶ ቅራኔን ያራባበታል። ቴክኖሎጂው ሊያስገኝ የሚችልውን ውጤታማ እንቅስቃሴ አስፈላጊ ላልሆነ አሳፋሪ ተግባር ማዋል እየተለመደ መጥቷል ። የወያኔ ሰርጎ ገብ የሶሻል ሚዲያ ሰራዊት (ኮካዎች) ሁን ተብሎ በተጠና መልኩ አጀንዳ በማቅረብና ደጋፊና ተቃዋሚ በመምሰል የዋሆችን በመማረክ የፈጠሩት ዋልጌነት ሳያንስ በተለይ ራሳቸውን የአማራ ሕዝብ ተቆርቋሪ አድርገው በሚያቀርቡ ወገኖች ከእለት እለት እየተዘወተረ የመጣው በሃሳብ የተለየን ግለሰብና ቡድን ለማየት በሚቀፍ የቃላት ጋጋታና ፤ ለማድመጥ የሚሰቀጥጥ ስድብ የተሞላ ዘመቻን ማካሄድ እንደ ትግል ስልት በመቁጠር በጭፍንና በመንጋ በገባቸውም ሆነ ባልገባቸው ጉዳይ እየተነሱ የሳይበር ጦርነት ማካሄድን ስራዬ ብለው ተያይዘውታል።

ስድብ የሃሳብ እጦት ነጸብራቅ ነው። ስድብ የተሸናፊነት ዋሻ ፡ የሰንፎች ጋሻና በራሱ የማይተማመን ደካማ ግለሰብና ቡድን ትጥቅ ነው። ስድብ የሓጥያት ፍሬ ፤ የሴይጣን መዝሙር ነው። አሉባልታ የባልቴቶች ወግ ፤ የቀጣፊዎች ማጥቂያ ፤ የተንኮለኞች ማምለጫ መንገድ ነው። በታላቁ

የሕይወት መጽሃፍ ፡ *በመጽሃፍ ቅዱስ መሰረት ስድብ እጅግ በጣም ከባድ ከሚባሉት ወንጀሎች ውስጥ ይካተታል! « ለቀደሙት አትግደል እንደተባለ ሰምታችኋል፤ የገደለም ሁሉ ፍርድ ይገባዋል። እኔ ግን እላችኋለሁ፤ በወንድሙ ላይ የሚቆጣ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል፤ ወንድሙንም ጨርቅ ለባሽ የሚለው ሁሉ የሸንጎ ፍርድ ይገባዋል፤ ደንቆሮ የሚለውም ሁሉ የገሃነም እሳት ፍርድ ይገባዋል። ይላል። ማቴ (5 ፤ 21-23)*

ሊቃውንት ‘’በሮማ ስትኖር እንደ ሮማዊ ሁን እንዲሉ’’ የሃሳብ ብዝሃነት ፤ የመደራጅት ነጻነት በምልዓትና በስፋት በተንሰራፋበት ሃገር እየኖሩ እንደ ስብስቴ ዘመን የሚያስቡ የፖለቲካ አቀንቃኞች እጅ በመውደቁ በሃገር ውስጥ ሕዝባችን እያደረገ ያለውን የሞት ሽረት ትግል በተጠናከረ ሁኔታ አረድቶ ለለውጥና ለውጤት እንዲበቃ ማገዝ አልተቻለም። በተለይ በአሁኑ ወቅት ከሁሉ የከፋ የሕልውና አደጋ የተደቀነበት የአማራው ሕዝብ ለመደገፍ ተንስተናል የሚሉ ድርጅት ቢጤዎችና የሳይበር ፋኖ የስድብ ምንሽር ታጣቂዎች እየታየ ያለው ከመስመር የወጣ አካሄድ ከማሳዘን አልፎ የብዙዎችን አንገት እያስደፋ ነው።

ድርጅት ለመገንባት የፖለቲካ አቋምን በማህበረሰብ ውስጥ በጥልቀት ለማስረጽ እና ሕዝብን አንቅቶ በተቋም ደረጃ ለማሰባሰብ መቻል የስኬቱ ምንጭ ጨዋነት ፤ አዋቂነትና የአቋም ጽናትን አጣምሮ የሚጠይቅ ነው። ሊያታግል የሚችል አጀንዳ ፤ ሊያስኬድ የሚችል የስትራቴጂ አቅጣጫ ፤ በስሜት ሳይሆን በስሌት የተቀረጸ ፖሊሲ ፤ ጠላትን በመቀነስ ወዳጅን የማብዛትን አስተምህሮ ሲከተል ፤ የትግል ስልትና ታክቲክ የተላበሰ ሲሆን በብዛት ሳይሆን በጥራት ላይ ሲያተኩር ፤ እንኳን ወገንን ጠላትን መማረክ ይቻላል። አንዳንዶች ይህን መሰረታዊ መርሆ ተከትሎ ራዕያቸውን ለማስካት ችሎታና አቅም ሲያጥራቸው ሌሎችን በማውገዝ ደጋፊን ለማሰባሰብ የሚጥሩበት ሁኔታ በሃገራችን የፖለቲካ አደባባይ መታየት ከተለመደ ሰነባበተ። በዚህ ብኩንና ኋላቀር አያያዝ ስር ትግሉ በመውደቁ የሕዝብ ተነሳሽነትና ለተሳትፎ ዝግጁነት ቢኖርም ሁኔታውን ለመጠቀምና ሕዝብን ለማነቃነቅ አልተቻለም።

ወገኖቼ በሃሳብ ጥራትና የሕዝብን ፍላጎት መነሻ አድርጎ የሚካሄድ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ለግዜው አድካሚ ሊሆን ቢችል እንኳ ውሎ አድሮ ውጤታማነትን መቀዳጀቱ አይቀሬ ነው። ብዙ ሳንርቅ በሕወሓት ተንበርካኪነት የሚታወቀው ደካማ በሆኑ ግለሰቦች ይዘወር የነበረው ኦህዴድ ፤ ሳይታሰብ የድርጅቱ ታሪክ ተለውጦ ተስፋ እንዲጣልበት በቅቷል ። ለዚህ ያደረሰው የለማ መገርሳ አመራር ከሚወክለው የብሄር አጥር አልፎ አብዛኛውን የሃገራችንን ሕዝብ ልብ ሊማርክ መቻሉን አይተናል። ይህ ሕዝባዊ ድጋፍ መሰረቱ የሕዝብን ስሜትና ፍላጎት የተመረኮዘ አቅጣጫ ማሳየት መቻሉ ነው።

ዛሬ እንዲ ጎልቶ ለሚታየው የወጣቱ ቅጥ ያጣ የሶሻል ሚድያ ምግባር አልባነት መሰረት የጣሉትና ይህን አስነዋሪ ባህል ለትውልዱ አርዕያ በመሆን ያስተማሩት በአማራው ስም ቀድም ብለው የፖለቲካ ንግድ የጀመሩት የአሮጌው ስርዕት ሎሌዎች በአማራው ስም የዘሩት እንክርዳድ አስተሳሰብ ይህው ፍሬ አፍርቶ የትግሉን መድረክ በንትርክ የተሞላ እንዲሆን አሻራቸውን አኑረዋል። ትላንት በሰባዎቹ ‘’በቾ’’ (እናቾንፋለን) እና በ’’ሾ ‘’ (እናሾንፋለን ) እንድ ዓይነት ርዕዮተዓለም እየተከተለ ፤ በመሬት ላራሹ ተመሳሳይ መፈክር ስር ተሰልፎ የታገለ አንድ ወንድማማች ትውልድ ለዕልቂት የተዳረገው አንዱ የሌላውን ሃሳብ ለማክብር ፈቃደኛ ባለመሆኑ እንደነበር ታሪክ ምስክር ነው።

በተለይ ለወገንና ለሃገር የሚያስብ አማራ እንደወግና ልማዳችን ፤ እና አባቶቻችን እንዳቆዩል ትውፊት ጠላትን ለመቅጣት ታጥቆ ወደ ፍልሚያው ጎራ እየፎከሩና መውረድ ፤ አለያም ሃቅና ማስረጃን አንግቦ ፍትህ አደባባይ በድፍረት መገኘት እንጅ እንደንፍሮ ሳይበር ላይ ተጥዶ መቀባጠር አይደለም። ለነዚህ ትግል ማለት ስድብ የመሰላቸው አንዳንድ የዋሃንና ጥቂት ሴረኞች የሚያካሂዱት አሳፋሪ ተግባር ባለታሪኩን ፤ ሃገር ወዳዱን ጀግናውንና ኩሩው የአማራ ሕዝብ ባህል ፤ ልማድ ፤ ወግ ፤ እምነትና ስነልቦና ያልተከተለ ወፍ ዘራሽ አድራጎት በምንም መመዘኛ ተቀባይነት የለውም። ለአማራው መቆም እንዲህ በመተቻቸት አይደለም ፤ በልዩነትም አምኖ አብሮ መጓዝ ይቻላል። ይህ ካልሆነ ደግሞ የሃሳብ ልዩነት

ያለውን ወገን ሳይተቹና ሳይጣሉ ማለፍ ሌላ ስልጡን አማራጭ ነው። እንኩዋንስ ዘምቦብሽ እንዲሁም ጤዛ ነሽ እንዲሉ መበታተንና መነቋቆር ለወያኔ ትልቅ እድሜ ማራዘሚያው ነው የሆነው።

ለተቀማጭ ሰማይ ቅርቡ ነው እንዲሉ በምዕራቡ ዓለም በተደላደለ ህይወት የሚያጣጥምው አንዳንዱ ፖለቲከኛ የሚያቀርበው የቅንጦት አጀንዳና የውዝግብ ርዕስ ፤ ሕዝባች እየደረሰበት ያለውን መከራና ስቃይ ግምት ውስጥ ያላስገባ ነው። ከዚህም በላይ በሃገራችን የሰፈነውን ሠውበላ የትግሬ ነፃ አውጪ የአፓርታይድ አገዛዝ በቀጡ የተረዳም አይምስልም ። የኛ ነገር ተደራጅቶ ከመታገል ይልቅ በተቸትና በንትርክ የሌሎችን ሥራ ማወክ የመሆን ልማድ አብሮን ያደገ እስኪመስል በድርጅት ታቅፈው ትግል ከሚያደርጉ ሃይሎች እጥፍ የሚሆን የተቺና የተሳዳቢ መንጋ በዝቶ መታየቱ አንዱ መገለጫ ይመስለኛል ።

በተለይም ለዚህ መጣጥፍ ምክንያት የሆነኝ የማህበራዊ ሚድያውን ትውልዱ እየተጠቀመበት ያለው አካሄድ ለሃገርም ለሕዝብም የማይጥቅም አፍራሽ እንቅስቃሴ እያሳደረ ያለው ተጽእኖ አደገኛ በመሆኑ ነው። ካለብን መጠነሰፊ ሃገራዊና ሕዝባዊ ችግሮች አንጻር በአሁኑ ወቅት የተቀጣጠለውን ሁለገብ ትግል የመምራት የማስተባበርና የመታገል ግንባር ቀደም ሃላፊነት ካለበት ይህ ትውልድ ውስጥ ፊታውራሪ መሆን የሚገባቸው አንዳንድ አዋቂ ነን ባይ አክቲቪስት የሚል ካባ የደረቡ ወጣቶች በየገጾቻቸው የሰለጠነ ውይይት ላይ የተመሰረተ የሃሳብ ፍሰትን ከመጋበዝ ይልቅ ለንትርክ ለውዝግብና ለስድብ የበለጠ መድረኩን ሲያውሉት ይታያል።

እንዳለመታደል ፖለቲካቸን ውይይትን ሂስና ግለሂስን የማስተናገድ ባህል ስለሌለው የስማ በለው የአሉባልታ ባህል እንዲዳብር በማድረጉ ሠፊና ጥልቅ ማህበራዊ ጉዳት አስከትላል። ከዚህም አንጻር ማህበራዊው ሚድያ ሃሳብን በነጻነት ለመግለጽና ለማንሸራሸር የተመቸ በመሆኑ ማንም የፈለገውን ሓሳብ በተረዳው መልኩ መግለጹ ዲሞክራሲያዊ መብት በመሆኑ ባከብርም ፤ በዚህ የጭለማ ግዜ ጥያቄያችን ወርዶ ወርዶ እንደ ሕዝብ የመኖርና ያለመኖር ደረጃ አዘቅት ውስጥ በወደቀበት ሁኔታ ላይ እያለ ዳር ቆሞ መመጻደቅ ጸጉር መሰንጠቅና መሰዳደብ ከሞራል አኳያ ተገቢ አይደለም። በአሮጌ አቁማድ አዲስ ወይን ጠጅ እንደማይሆን ሁሉ የሃስብ ዝውውር የመረጃ ስርጭት ግዜ ቦታ ሳይገድበው በቀላሉ ለሁሉም በማድረስ በገንቢ ሃሰቦች ሕዝብን በጋራና በፍቅር ማስለፍ እንድሚቻልና እንደተቻለ ሁሉ ፤ የጥላቻ የከፋትና የሃሰት ወሬዎች ሕዝብን ሊያጫርስ ሃገርንም ሊያፈርስ የሚቸልበት ከባድ አቅም ያለው በመሆኑ የሶሻል ሚድያውን አጠቃቀም በተገቢው እንዲሆን ትውልዱን ከዚህ አድራጎት ለማራቅ የሁሉም ወገን ሃላፊነት ይሆናል።

ከሁሉም በላይ ስድብ በባሕሉ እጅግ ነውር የሆነውን የአማራውን ነገድ ወክሎ በድርጅት ይሁን በግለሰብ ደረጃ በሃሳብና በአቋም የተለየን ቡድን ሆነ ግለሰብ መዝለፍ ፤ የሃሰት አሉባልታ ማራገብ ፤ የአማራውን ማህበረሰብ ማዋርድ አባቶቻችን ያኖሩትን የከበረ የጨዋነት ታሪክ መናድ መሆኑን በአጽኖት ማስገንዘብ ያስፈልጋል። ወንድነት በማይፈተሸበት ተግባራዊ ስራ በማይታይበት በስደት አገር ተቀምጦ ከእስክሪን ጀርባ በመንጋ አድፍጦ ማቅራራትና የራስን ስብዕና ለመገንባት የባጥ የቆጡን መዘባረቅ የታጋይነት መለኪያ አይደለም። ትግሉን ከመጎተት ያለፈ ሚናም የለውም። አማራነት መገለጫው ተግባር እንጂ ስድብ አይደለም ። ወጣቱ ተምሳሌቶቹን አስራት ወልደየስን ፤ ጎቤ መልኬን ፤ ደመቀ ዘውዱን ተመልከት እነዚህ ሰማዕቶች እንኳን ወገናቸውን የሚታገሉትን ጠላት እንኳ አክብረው በጨዋ ቋንቋ በሃስብ ጥራትና በትህትና አቋማቸውን ሲንጸባርቁ ነው የሚታወቁት። ሞትን የናቁት እስር ያላንበረከካቸው ጀግኖቹ ወንድሞቼ እስክንድር ነጋ ፤እንዲለም አራጌ ፣ አበበ ቀስቶ አኔ እስከማቃቸው ድረስ የሚታገሉትን አገዛዝና መሪዎች እንኳ ስማቸውን ሲያነሱ እጅግ ተጠንቅቀው ኢትዮጵያዊ ጨዋነትን መሰረት አድርገው እንደነበር ለማስታወስ እገደዳለሁ።

የኦሮሞ ወጣት (ቄሮ) ተደራጅቶ ተናቦና ተስማምቶ ሕዝባዊ ድልን እየተቀዳጀ ፤ ክልሉን ከሕወሃት ተጽዕኖ ነጻ አድርጎ ቢያንስ ዛሬ ያለፍርሃት ሃሳቡን በአደባባይ መግለጽ ችሏል። ጀግኖቹንም በደማቅ ስነስርአት እንዴት እንዳስተናገደ አይተናል። የክልሉን ካድሬና ታጣቂን ከጎኑ አሰልፎ አንድነቱን በአደባባይ አስመስክሯል። ይህ ድል በውጭና በሃገር ውስጥ ያሉ የኦሮሞ ብሔር አባላት በትብብርና

በተግባር ቆመው ያገኙት ውጤት ነው። ቄሮ ማህበራዊ ሚድያውም ለዚህ ውጤት እንዲበቃ በተገቢው ተጠቅሞበታል እኛ በውጭ ያለነው አማራውቹ ከዚህ ወንድም ማህበረሰብ ልምድ ቀስመን በጋራ ልቆም ይገባል። እውነት ለመናገር በዛሬው እለት ወያኔ ኤንባሲ በወልድያ የተፈጸመውን ግፍ ለመቃወም የተገኘው ሕዝብ ቁጥር የሚያስዝን ብቻ ሳይሆን የሚያስፍርም ነው። ፌስቡክ ላይ ተጥዶ ሌላውን የሚዘልፈው ግን ቁጥሩ ብዙ ነው። ይህ መጤና አጉን ባህል በግዜ ካላስወገድነው ጉዳቱ አደገኛ ነው። ።

ስድብ አሉባልታና ወሬ ድላችንን ያስነጠቀ ፤ ተቋሞቻችንን የናደ እጅግ አደገኛ ወረርሽኝ ነው። በተለይ በሰሜን አሜሪካ የትላንቱ ቅንጅት ተበታትኖ እንዲጠፋ ፤ ያን የመሰለ የምሁራን ተሳትፎ እንዲመክን ያደረገው ይህው እሳፍሪና እርካሽ የወሬ ወረርሽኝ ነው። ዛሬ ለዚህ ነው የምሁራኑ ተሳትፎ ነጥፎ የዲያስፖራው ትግል የልጆች መቀለጃ የሆነው ።ሰዎች በአቅምና በችሎታቸው ለሃገራቸውና ለወገናቸው በሚችሉት አቅም አስተዋጽዖ እንዳያበረክቱ በስድብና በስም ማጥፋት ጋሬጣ መንገዱ የታጠረ በመሆኑ ምሁራን ወደ ትግሉ እንዳይቀላቀሉ የራሱን ተጽዕኖ አሳድሯ። ዛሬ ሕዝባችን ውጤት እርቆት ከተቃዋሚው አምባ ተስፋ ቢያጣ ከአገዛዙ ሰፈር ካሉ ተራማጆች ለውጥን እየጠበቀ ይገኛል ። በዚህ ግዜ ሃገር ውስጥ ለሚካሄደው ትግል ከድጋፍ ሰጪነት የዘለለ ሚና የሌለው በምዕራቡ ዓለም ያለው የፖለቲካ አክቲቪስት ሆነ ድርጅት ቢያንስ ሕብረት መፍጠርና በጋራ መታገል ባይችል ተከባብሮ ሊቆም ሊያቅተው ባልተገባ ነበር።

አምላክ አስተዋይ ልቦናን ያድል!!!